# ኃይል መቆጠብ

## እንዴት ነው የሚሠራው? ጥቅሞቹ ምንድናቸው?



# ኃይል መቆጠብ ምንድነው?

ኃይል ሲቆጠብ አንድ ሕንጻ አነስተኛ ኃይል በመጠቀም እንዲሠራ ይረዳል።

ኃይል ቆጣቢነትን ማሻሻል ኃይልና ገንዘብ ይቆጥባል።

እና ማይክሮግሪድ ለመሥራት የመጀመሪያው እርምጃ ነው!





# አምፖሎችን ይቀይሩ

የLED አምፖሎች ከመደበኛ አምፖሎች 75% ያነሰ ኃይል ይጠቀማሉ!

ኃይልን መቆጠብ ገንዘብን ይቆጥባል!

# መከላከያ ሽፋን

ግድግዳዎችዎና ጣሪያዎ ውስጥ የመከላከያ ሽፋን ማስገባት የውጪ አየር ሙቀት ውስጥ ያለው አየር ሙቀት ላይ ተጽዕኖ እንዳይፈጥር ያደርጋል።

በበጋ ወቅት አፓርተማዎ ኢንዲቀዘቅዝ ለማድረግ ኤሲዎ ተጨማሪ ሥራ መሥራት አያስፈልገውም!

ያነሰ ኃይል መጠቀም ገንዘብ ይቆጥባል!





# ክፍተቶችንና ስንጥቆችን ያሽጉ

በቀዳዳዎችና በክፍተቶች በኩል ወደ ሕንጻ ውስጥ የሚገባ ወይም ወደ ውጪ የሚሾልክ አየር ኃይል እንዲባክን ያደርጋል።

ከቤትዎ አየር እንዳይሾልክ ቤትዎን ያሽጉና የውስጡን ምቾት ያሻሽሉ እንዲሁም ኃይል ይቆጥቡ።

# መስኮቶች

ሁሉም መስኮቶች እኩል አልተፈጠሩም!

በማያስገባ ጋዝ የተሞሉትን ድርብ ወይም ባለሶስት መስታወት መስኮቶች ቤትዎ በክረምት ምቹና በበጋ ወቅት ቀዝቀዝ ብሎ መቆየቱን ያረጋግጣሉ።

በመስኮቶችዎ ዙሪያ አየር እንዳሾልክ ማሸጉን አይርሱ!





# መገልገያ መሣሪያዎች

አሮጌ መገልገያ መሣሪያዎች ብዙ ኃይል ይጠቀማሉ። እነሱን መተካት ኃይልና ገንዘብ ሊያድን ይችላል!



አዲስ ፍሪጅ፥ ሰሃን ማጠቢያ፥ ልብስ ማጠቢያ፥ ወዘተ. ሲገዙ የ Energy Star (ኤነርጂ ስታር) ደረጃ እንዳላቸው ያረጋግጡ።

# የውሃ ማሞቂያዎች



የአየርና የውሃ ማሞቂያዎችን ሲተኩ ኃይል ቆጣቢና በኤሌክትሪክ የሚሠሩትን ለመምረጥ ከሠራተኛው ጋር አብረው ይሥሩ።

ለእነሱ የገንዘብ ማበረታቻዎችና ቅናሾች አሉ!

ኃይል ቆጣቢነት ለከባቢ
አየሩና ለሒሳቦችዎ ጥሩ
ነው!